አሐዱ:ባንክ
Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com


# ንግድና ልማት

ነሐሴ 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com


## አዲስ ቻምበር በ2016 አ.ም ተደራሽነቱን ይበልጥ ለማስፋት እንደሚሰራ የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት ገለጹ



በስታፍ ሪፖርተር

የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት መሰንበት ሽንቁጤ የ2016 አ.ም አዲስ አመትን አስመልክተው ከምክር ቤቱ ሚዲያ ጋር ቃለምልልስ አካሂደዋል፡፡ ከ2015 አ.ም በፊት የነበሩ ተግዳሮቶች እንደ ኮቪድ 19 የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ተጭነውናል፤ የምክር ቤቱ አንዱ ምሰሶ አባላቶቹ ናቸው መዋጮ መክፈላቸው ብቻ ሳይሆን የነሱን ውጤት ማየት የምንፈልገው ነው በማለት ባደረጉት ቃለምልልስ ወቅት ተናግረዋል፡፡ ምክንያቱም ሀገር ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ጠንካራ የግል ዘርፍ ሲኖር ነው ብለዋል፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## አዲስ ቻምበር በ2016 አ.ም የሚያካሂዳቸውን ንግድ ትርዒቶች መስከረም 8 2016 ዓ.ም ይፋ እንደሚያደርግ አስታወቀ



(አዲስ ቻምበር) መስከረም 3 2016 አ.ም አዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከሚያከናውናቸው አበይት ተግባራት መካከል የተለያዩ ዓለምአቀፍ የንግድ ትርዒቶችን ማዘጋጀትና ማካሄድ አንዱ ሲሆን፣ በዚህም ለሀገራችን የንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት ቁልፍ ሚና በመጫወት ላይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የጫት ወጪ ንግድ የ36 በመቶ ገቢ ቅናሽ አሳየ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በተጠናቀቀው በጀት ዓመት 31,363.5 ቶን የጫት ምርት ወደ ተለያዮ መዳረሻ ሀገራት በመላክ 248. 36 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱ ገለፀ፡፡

በ2015 በጀት አመት ሶማሊያ፣ጅቡቲ፣ እስራኤል፣ ኬንያ፣ ሴራሊዮን፣ ኮንጎ፣ ማዳጋስካር አና ብሩንዲ የሀገሪቱ የጫት ምርት የተላከባቸው መዳረሻ ሀገራት ናቸው፡፡

ከጫት ምርት የተገኘው ገቢ ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በመጠን የ44.24 በመቶ እንዲሁም በገቢ በመቶኛ 36.7 ቅናሽ ያሳየ ሲሆን ለዚህም ኮንትሮባንድ፣ ተደራራቢ የታክስ ክፍያ፣ የንግድ ስነምግባር ጉድለት፣ ከጉምሩክ እውቅና ውጪ አላስፈላጊ ኬላዎች መስፋፋት ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እንዲቀንስ ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ተጠቃሽ ናቸው ነው ያለው ንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፡፡

ወደ ገጽ 3 ዞሯል



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

## በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ነሐሴ 2015 እትም

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

# ርዕሰ አንቀጽ

## ጠንካራና የተባበረ ተቋም ለግሉ ዘርፍ እድገት

ዘላቂ ተቋማት በራሳቸው የሀገር እድገት ማሳያ መስታውቶች ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የንግድ እና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች ደግሞ እንደ ተቋም የንግዱን ማህበረሰብ በመወከል የሚመሰረቱ ተቋማት ሲሆኑ የህልውናቸው መሰረትም አባላቶቻቸው ናቸው።

እነዚህ ተቋማት ግለሰብ ነጋዴን ጨምሮ በልዩ ልዩ የንግድ ስራዎች ላይ የተሰማሩ የንግድ ድርጅቶችን በአባልነት የሚያካትቱ ሲሆኑ የአባላቶቻቸውን ጥቅሞች ለማስጠበቅ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በቅርበት መወያየት ተቀዳሚው ዓላማቸው ነው።

አዲስ ቻምበርም በአንጻሩ ከእድሜ እኩዮቹ ከአዲስ አበባ ንግድ ስራ ት/ቤት፣ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ፣ ከመርከብ ድርጅት እና ከመሳሰሉት ጋር ተፈጥሮ እየተጓዘ የዘለቀ አንጋፋ የሀገሪቱ አለኝታ ነው ማለት ይቻላል። የሰራቸው ሀገራዊና ተቋማዊ ስራዎቹ ለቀጣዩ ትውልድ በታሪክ ሲታወሱ የሚኖሩ ናቸው። ታዲያ አዲስ ቻምበር እያስመዘገበ ላለው ተቋማዊ ጥንካሬና አሁን ለደረሰበት ደረጃ አባላቱ እና ባለድርሻ አካላቱ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ የንግድ ምክር ቤቶች ታሪክ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፈው አዲስ ቻምበር ፋና ወጊ ብቻ ሳይሆን በሥራዎቹም አርአያ ለሌሎችም ምክር ቤቶች መቋቋም መሠረት ነው ። ንግድ ምክር ቤቱ አሁንም የንግዱን ማኅበረሰብ ጥቅም ለማስከበርና ተፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ አገልግሎቶችን በተሻለ ብቃት ለማቅረብ እንዲያስችለውና ተቋማዊ ቁመናውን በሁለገብ መልኩ እየገነባ ነው።

ተቋሙ ከሚያከናውናቸው በርካታ የንግድ ድጋፍ አገልግሎቶች፤ የግንኙነት ተግባራትና የአድቮኬሲ ሥራዎች ዘመኑን ተከትሎ ለማከናወን አሁን ላይ በአደረጃጀት ተሻሽሎና ዘምኖ በሰው ኃይል ተጠናክሮና በፋይናንስ አቅም ጐልብቶ ለአባላቱ የተሻለ አገልግሎት በመስጠት ላይ የመገኘቱ ሚስጥር በዋናነት የአባላቱ አስተዋጽኦ ነው ።

እያካሄዳቸው ያሉትን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች እያደገ ከመጣው የንግዱ ማኅበረሰብ ፍላጎትና ለውጥ ጋር ለማጣጣም የሚያስችሉ የተለያዩ ተቋማዊ እርምጃዎችንም በመውሰድ ላይ ይገኛል።፡በአዲሱ አመትም እያንዳንዱ አባል ለምክር ቤቱ ያለውን ድጋፍ የሚያጠናክርበትና እንደየአቅሙ የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያበረክትበት አመት ይሆናል። ንግድ ምክር ቤቱ ያለ አባላቱ ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ እዚህ ሊደርስ አይችልምና።

በተለይም ለንግድ እና ኢንቨስትመንት ምቹ ከባቢ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ፤ የንግዱን ሕብረተሰብ በአገሪቱ የኢኮኖሚዊ ዕድገት ድርሻውን ከፍ ለማድረግ እና ጠንካራ የቢዝነስ ዘርፍ እንዲፈጠር ንግድ ምክር ቤቱ አበክሮ ይሰራል።

ንግድ ም/ቤቱ የተጣለበትን ከፍተኛ ሃላፊነት ለመወጣት ያስችለዉ ዘንድም ሁልጊዜም የአገልግሎት ብቃቱን፤ የንግዱን ህብረተሰብ የመወከል አቅሙን ለማሳደግ ስር ነቀል ለውጦችን በማድረግ ይቀጥላል። በተለይም ከመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀራረብ በትልልቅ እና አንኳር ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ቀጣይነት ያለው እንቅስቃሴ ለማድረግ አባላቱና ባለድርሻ አካላት ከፍ ያለ ሚናቸውን መወጣት አለባቸው።

የግሉም ዘርፍ ዋነኛ የኢኮኖሚ ሞተር ሆኖ እንዲቀጥልም የምክር ቤቱ አመራርና አባላት ማኔጅመንትና ሰራተኞች እንዲሁም ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በ2016 ለተያዘው እቅድ እና ለሚመዘገበው የስራ ውጤት እጅና ጓንት ሆነው ይሰራሉ። ጠንካራና የተባበረ ተቋም ለግሉ ዘርፍ እድገት ወሳኝ ነውና!!!!

# የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ተቋማቂ ዘላቂነትን እውን ለማድረግ ሰራተኞች የበለጠ ተግተው እንዲሰሩ መልእክታቸውን አስተላለፉ

(አዲስ ቻምበር ነሀሴ 17 2015 አ.ም) ከሰባት አስርት አመታት በላይ የንግዱን ማሕበረሰብ በማገልግል ፈር ቃድጅ የሆነው አዲስ ቻምበር ዛሬ ላይ በሺዎች የሚቆጠሩ አባላትን በማቀፍ ጠንካራ የግል ዘርፍ እውን እንዲሆን በርካታ አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛል። ምክር ቤቱ የጀመረውን የትውልድ ቅብብሎሽ በዘላቂነት ለማስቀጠል ሁሉም ሰራተኞች ተግተው መስራት እንዳለባቸው ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ የምስጋና መልእክታቸውን ባስተላለፉበት ወቅት ተናግረዋል።

የቦርድ አባላትን በመወከል የምስጋና ንግግር ያደረጉት ወ/ሮ መሰንበት ምክር ቤቱ በርካታ ተግዳሮቶችን በመቋቋም ለስኬት መብቃቱ የሚደነቅ ነው ብለዋል። የተቋም ዘላቂነትን ለማረጋገጥ ሰራተኞች በጥምረትና በቡድን መንፈስ የመስራት ባህልን በማጠናከር በመጪው አዲስ አመት የበለጠ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ጥሪ አቅርበዋል።

በዚህ የምስጋና ቀን ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ዋና ጸሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም ምክር ቤቱን ተወዳዳሪና ዘላቂ ተቋምን ለመፍጠር የሚያስችል መዋቅር ተግባራዊ መደረጉን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ተወዳዳሪ የግል ዘርፍ እውን እንዲሆን ምክር ቤቱ በ2015 አ.ም የቢዝነስ ኢኖቬሽንና የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት አገልግሎቶችን መጀመሩን ያስታወሱ ሲሆን ይህ ትልቅ ስኬት እንደሆነና በምክር ቤቱ የተመዘገቡ ስኬቶች የተቀናጀ አሰራር ውጤት መሆኑን ዋና ጸሀፊው አክለው ተናግረዋል።

በመጨረሻም ሰራተኞች ምክር ቤቱ ያስቀመጣቸውን ግቦች ለማሳካት በትጋት እንዲንቀሳቀሱና በፕረዚደንቷ የተላለፉ ቁልፍ መልእክቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# አዲስ ቻምበር በ2016 አ.ም ተደራሽነቱን ይበልጥ ለማስፋት እንደሚሰራ የአዲስ ቻምበር ፕረዚደንት...

**ከ ገጽ 1 የዞረ**

እንደ ንግድ ምክር ቤት 2015 አ.ም ከሞላ ጎደል ውጤታማ አመት ነበር ለማለት እንችላለን ያሉት ፕረዚደንቷ በአንድ በኩል የግሉ ዘርፍ እንደ ኮቪድ 19 ከመሳሰሉ ተግዳሮቶች ከሚስከትላቸው ኢኮኖሚዊ ጉዳቶች እንዲያገግም እና ንግድ እንዲቀጥል ምክር ቤታችን ትልቅ ስራ ሰርቷል ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ለንግዱ ማህበረሰብ የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት እና ቢዝነሳቸውን በዘላቂነት እንዲያስቀጥሉ የሚያስችሉ ድጋፎች ምክር ቤቱ መስጠቱን ተናግረዋል።

ሌላው በ2015 አ.ም የንግዱን ማህበረሰብ ወይም የምክር ቤቱ አባላትን ለመደገፍ ከሰራናቸው ስራዎች መካከል የንግዱ ማህበረሰብ የሚያጋጥማቸው የተለያዩ ተግዳሮቶች በመንግስት በኩል መፍትሄ እንዲሰጣቸው የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራዎች እንደተሰሩ የገለጹ ሲሆን ከነዚህም መካከል የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን ለውይይት በማቅረብ ምክረሀሳቦች እንዲካተቱ በማድረግ ለፖሊሲ የሚሆኑ ግብአቶችንና ምክረ ሀሳቦችን ጠቅሰዋል። እነዚህ ምክረሀሳቦች መንግስት በመጪው ጊዜ በእቅድ ውስጥ እንዲካተቱና ተግባራዊ እንዲደረጉ ጥረት አድርገናል ብለዋል። እነዚህ ምክረሀሳቦች የነጋዴው መብትና ጥቅም እንዲከበር የተረጋጋ ሀገርና ኢኮኖሚ እንዲፈጠር የበኩላቸውን አስተዋጾ ያደርጋሉ ብለን እናምናለን በማለት ገለጸዋል። በ2015 አ.ም እንደ ንግድ ምክር ቤት ካከናወናቸው ስራዎች መካከል የንግዱ ማህበረሰብ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ተቋማትን እውን ማድረግ ነበር ያሉት ፕረዚደንቷ ከነዚህም መካከል የኩባንያ መልካም አስተዳደርን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎችን ሰርተናል በማለት ተናግረዋል፡፡ በተለይም በግሉ ዘርፍ አከባቢ ኩባንያን በመልካም አስተዳደር እንዲመራ የሚያስችል አቅምና እውቀት ስለሌለ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ አይነት አወቃቀሮች በዘመድና በጓደኛ የመሞላት አጋጣሚዎች ይከሰታሉ። ስለዚህ ተቋማት የቦርድ አወቃቀራቸው ከችሎታ ይልቅ በዝምድና ላይ የተመሰረተ ይሆንና የሚፈለገው ውጤት አይመጣም ወይም ኩባንያው ለማሳካት ያለመው እቅድ ሳይሳካ ይቀራል ብለዋል። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ንግድ ምክር ቤታችን ለመጀመርያ ጊዜ የዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩትን አቋቁሟል። የአመራር ብቃት ለኩባንያ ስኬታማነት ትልቅ ሚና አለው ያሉት ፕረዚደንቷ ይህን ተቋም በቅርቡ ትላልቅ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተወካዮች ባሉበት በይፋ አስጀምረናል ብለዋል።

ሌላው የ2015 ስኬታችን የቢዝነስ ኢንኩዩቤሽን ማእከልን እውን ማድረግ ነበር። ይህ አገልግሎት የሀገርን የስራ አጥነትን ችግር በመፍታት እና የሀገርን ኢኮኖሚ እንዲሻሻል በማድረግ ይህ ተቋም የሚኖረው ሚና ከፍተኛ እንደሆነ የገለጹ ሲሆን ይህ ተቋም የንግዱ ማህበረሰብ የሰለጠነ የሰው ሀይል እንዲያፈራ ፤ አቅም ያላቸው ስራ ፈጣሪዎች እድሉን አግኝተው ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስችል ተቋም ነው። ይህ ተቋም እንዲገነባ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እገዛ ወሳኝ ነበር ብለዋል።

ምክር ቤቱ የውስጥ አሰራሩን ለማሻሻልና ዘመናዊ ለማድረግ ባለው አቅም በርካታ ስራዎችን መስራቱን የገለጹት ፕረዚደንቷ ከነዚህም መካከል ለምክር ቤቱ አባላት ዘመናዊ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል አቅምን መፍጠር ሲሆን ይህ ለስራ አመቺ የሆኑ የቢሮ አደረጃጀቶችን በመፍጠር፤ የዲጂታል አገልግሎት ጅማሬዎችን እውን ማድረጋችን ካለንበት አውድ አንጻር ትልቅ ስኬት ነው ሊባል ይችላል።

ያለፉትን አመታት ስናይ በንግድ ምክር ቤቱና በተለያዩ የመንግስት ተቋማት መካከል ለምሳሌ በፕላኒንግ ኮሚሽን እና በምክር ቤታችን መካል ያለው ግንኙነት እንዲሻሻል በማድረግ የንግዱ ማህበረሰብ ለሀገር ግንባታና ልማት የሚያደርገውን አስተዋጾ ከፍ እንዲል ጥረት በማድረግ ላይ እንገኛለን ብለዋል። ይህ መልካም ግንኙነት የንግዱ ማህበረሰብ ምርቱን በአግባቡ እንዲያመርትና እንዲሸጥ በማድረግ ኢኮኖሚው እንዲረጋጋ የበኩሉን አስተዋጾ እንዲያደርግ ያስችለዋል።

በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ያለው ግንኙት እንዲጠናከር ምክር ቤታችን ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ያሉት የንግድ ምክር ቤቱ ፕረዚደንት እንዲህ አይነት ግንኙነቶች ተግባራዊ እንዲሆኑ ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ጋር የመግባቢያ ግንኙነቶችን በመፈራረም ተግባራዊ እንዲሆኑ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆኑ ተናግረዋል።

ምንም እንኳን ምክር ቤቱ በርካታ ስኬቶችን ያስመዘገበ ቢሆንም ተግዳሮች አይጠፉም ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የሰላምና ጸጥታ ሁኔታ መደፍረስ የንግዱ ማህበረሰብ ላይ ያስከተለው ተጽእኖ ከፍተኛ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን ምክር ቤቱ እነዚህ ችግሮች እንዲፈቱ ጥረት ያደርጋል፤የንግዱም ማህበረሰብ እነዚህን ተግዳሮቶች ተቋቁሞ የመስራት አቅምን መፍጠር አለበት ብለዋል።

ሌላው ከዚህ ጋር የሚያያዘው በዚህ መሀል ህገወጥ ንግድ ሲበራከት ህጋዊው ነጋዴ የሚጎዳበት አጋጣሚ ይፈጠራል ያሉት ፕረዚደንቷ እነዚህ ህገወጥ ነጋዴዎች ግብር አይከፍሉም፤ጥራት የጎደለው ምርት ለገበያ ማቅረብ የመሳሰሉ ድርጊቶች ህጋዊ ነጋዴውን ከውድድር ውጭ እንዲሆን እያደረጉት በመሆኑ ምክር ቤታችን በዚህ ላይ ብዙ ስራዎች ይጠብቁታል በማለት የ2016 አዲስ አመት መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# አዲስ ቻምበር ከአባላቱ እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የአብሮነትና የምስጋና ቀንን አከበረ



**በስታፍ ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ እያስመዘገበ ላለው ተቋማዊ ጥንካሬና አሁን ለደረሰበት ደረጃ አባላቱን እና ባለድርሻ አካላትን አመሰገነ። አዲስ ቻምበር ከአባላቱ እና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የአብሮነትና የምስጋና ቀንን በባለፈው ነሀሴ 18 2015 በስካይላይት ሆቴል በድምቀት አክብሯል። በእለቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የአዲስ ቻምበር ዋና ጸሃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም እንደተናገሩት በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪካ የንግድ ምክር ቤቶች ታሪክ ከቀዳሚዎቹ ተርታ የሚሰለፈው አዲስ ቻምበር ፋና ወጊ ብቻ ሳይሆን በሥራዎቹም አርአያ ለሌሎችም ምክር ቤቶች መቋቋም መሠረት ነው ማለት እንችላለን ብለዋል።

ለዚህም ስኬት አባላቱና የባለድርሻ አካላት ሚናቸው ከፍተኛ ነበርና እናመሰግናለን ሲሉ ተደምጠዋል። ንግድ ምክር ቤቱ የንግዱን ማኀበረሰብ ጥቅም ለማስከበርና ተፈላጊ የሆኑ ዘመናዊ አገልግሎቶችን በተሻለ ብቃት ለማቅረብ እንዲያስችለውና ተቋማዊ ቁመናውን በሁለገብ መልኩ እየገነባ ነው ብለዋል።

የአዲስ ቻምበር ፕሬዚዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ ባሰሙት የመክፈቻ ንግግር አዲስ ቻምበር ከሚያከናውናቸው በርካታ የንግድ ድጋፍ አገልግሎቶች፣ የግንኙነት ተግባራትና የአድቮኬሲ ሥራዎች ዘመኑን ተከትሎ ለማከናወን አሁን ላይ በአደረጃጀት ተሻሽሎና ዘምኖ በሰው ኃይል ተጠናክሮና በፋይናንስ አቅም ጐልብቶ ለአባላቱ የተሻለ አገልግሎት በመስጠት ላይ የመገኘቱ ሚስጥር በዋናነት የአባላቱ አስተዋጽኦ ነው ብለዋል።

እያካሄዳቸው ያሉትን ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች እያደገ ከመጣው የንግዱ ማኀበረሰብ ፍላጎትና ለውጥ ጋር ለማጣጣም የሚያስችሉ የተለያዩ ተቋማዊ እርምጃዎችንም በመውሰድ ላይ ይገኛል ብለዋል። በመጪዎቹ ዓመታት እያንዳንዱ አባል ለምክር ቤቱ ያለውን ድጋፍ እንዲያጠናክርና እንደየአቅሙ የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት አሻራውን እንዲያኖር ጥሪ አቅርበዋል።

ንግድ ምክር ቤቱ ያለ አባላቱ ተሳትፎ እና አስተዋጽኦ እዚህ ሊደርስ አይችልም ነበር ያሉት ፕሬዚዳንት መሰንበት ብዙዎች የደከሙለት ሥራ ዛሬ ፍሬ አፍርቶ ስናይ ደስታችን እጥፍ ድርብ ነውና ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለነበራቸው አብሮነት እናመሰግናለን ብለዋል። በአብሮነት እና በምስጋና ቀን ክብረ በአል ላይ ከ150 በላይ አባላት፣የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣የቻምበር ማኔጅመንትና ሰራተኞች፣የዲፕሎማቲክ አባላት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ታድመዋል።

አባላቱም የአዲስ ቻምበር አባል በመሆናቸው ያገኟቸውን ጥቅሞች በማንሳት ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ከነዚህም መካከል የኤችኤስቲ ፓርትነርስ መስራችና ሊቀመንበር አቶ ሰለሞን ግዛው፣ የሞሃን ኢንቨስትመንት ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ ሃርሽ ኮታሪ ይገኙበታል። በእለቱም የህንድ እና የኢትዮጵያን የንግድ ግንኙነት የተመለከቱ መረጃዎች ለታዳሚው ቀርበዋል።

## አዲስ ቻምበር በ2016 አ.ም የሚያካሂዳቸውን ንግድ ትርዒቶች...

ከ ገጽ 1 የዞረ

ከዚህ አንፃርም ምክር ቤቱ በ2016 አ.ም በጀት ዓመት ውስጥ የሚያካሂዳቸውን ንግድ ትርዒቶች ለሀገር አቀፍ እና ለዓለምአቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ለአጋር ድርጅቶች እና ሌሎች ባላድርሻ አካላት የሚያስተዋውቅበት ይፋ ማድረጊያ ፕሮግራም መስከረም 8 ቀን 2016 ዓ.ም እንደሚያካሂድ ያስታወቀ ሲሆን በዚህ አመት የሚካሄዱት የንግድ ትርኢቶች ተለይተዋል።

በዚህም መሰረት ከሕዳር 27 እስከ 29 ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ የሚካሄደው 14ኛው አዲስ ቻምበር የእርሻና ምግብ ዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒት፤ ከየካቲት 14 እስከ 18 ቀን 2016 ዓ.ም የሚካሄደው 26ተኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ ንግድ ትርዒት እና ከግንቦት 15-19 ቀን 2016 ዓ.ም 6ኛው አዲስ ቻምበር ዓለምአቀፍ የማኑፋክቸሪንግና ቴክኖሎጂ ይገኙበታል።

በአመቱ የተለዩ የንግድ ትርኢት መርሀግብሮችን በተሳካ ሁኔታ ለማዘጋጀት ምክር ቤቱ ከወዲሁ የዝግጅት ስራዎችን እያከናወነ መሆኑ ተገለጿል።

# ንግድ ም/ቤቱ ለአቅመ ደካሞች የበዓል መዋያ ድጋፍ አደረገ





**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት አዲስ ቻምበር ለንግዱ ማህበረሰብ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች በተጨማሪ ማህበራዊ ሃላፊነትን በመወጣት ረገድ በርካታ ስራዎችን ሰርቷል። ከነዚህ መካከል በአዲስ አበባ ከተማ ለሚገኙ አቅመ ደካማ ዜጎች የሚያደርገው ድጋፍ አንዱ ነው። ምክር ቤቱ የ2016 አ.ም አዲስ አመትን አስመልክቶ በቦሌ ክ/ከተማ በመገኘት ከ100 በላይ ለሚሆኑ ድጋፍ ለሚሹ የበዓል መዋያ ስጦታ አበርክቷል።

በሥነ ስርዓቱ ላይ የንግድ ም/ቤቱ ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ የንግዱ ሕብረተሰብ ያደረገው እርዳታ የዘመን መለወጫ በዓል ካለን ላይ በማካፈል ከወገኖቻችን ጋር በጋራ እናከብራለን ከሚል በጎ ዕሳቤ የመነጨ ነው ብለዋል።

በክፍለ ከተማው ከ14 ወረዳዎች ለተውጣጡ ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው 3ሊትር ዘይትና 5 ኪሎግራም ዱቄት እንዲደርሳቸው መደረጉን ለመረዳት ተችሏል።

# አዲስ አመትና እቅድ!




**በከፍያለው ዋሲሁን**

አዲስ ዓመትን በምንቀበልበት ዋዜማ ላይ እንገኛለን ፡፡ ኢትዮጵያ ዘመንን አስልታ መቁጠር ከጀመረች እነሆ 2016 ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ዘመኖች ብቻ ሳይሆኑ በርካታ የሰው ልጆች ኑሮው አልፈዋል፡፡ በእነዚህ አመታት በርካታ ለትውልድ የሚተላለፉ ስራዎች ተሰርተው ዛሬ ላይ ደርሰናል፡፡ ይህው አምና አዲስ ዓመት ብለን የተቀበልነው 2015 ኢ.ም አሮጌ ተብሎ ሊሸኝ በጣት የሚቆጠሩ ቀናቶች ቀርቶታል፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች የዓለም አገራት በተለየ የራሷ የዘመን ስሌትና ቀመር ያላት አገር ናት፡፡ ብቸኛዋ የአስራ ሦስት ወር ፀጋ ባለቤት አገር መሆኗም ይታወቃል፡፡ ታዲያ አስራ ሦስተኛው የጳግሜ ወር አብቅቶ የአዲሱ ዓመት መባቻ የሆነው የመስከረም ወር ሲባጅ ብዙዎቻችን አዳዲስ የሕይወት ዕቅዶችን ማውጣት ወይንም የጀመርነውን አጠናክረን በመቀጠል ውጤታማ ለመሆን እናስባለን፡፡ ዘመን ዕለቱን ጠብቆ ሲቀየር የእኛም የአስተሳሰብ፣ አመለካከትና አጠቃላይ የሕይወት ዘይቤና እሳቤ እንዲቀየርም እንተልማለን፡፡

አዲስ ዓመት ደስ የሚል ወደ ተስፋና ብርሃን የምንሄድበት በዓል በመሆኑ ለኹሉም ኢትዮጵያዊ ትልቅ በዓል ነው፡፡ ኹሉም በደስታ የሚያከብረውና ጓጉቶ የሚጠብቀው በዓልም ነው፡፡ በእርግጥም አዲስ አመት ተስፋ ነው፡፡ አዲስ ነገር የሚወጠንበት ፣ አዲስ መሆኑ ፣ ለአዲስ ስራ በአዲስ መንፍስ ሁሉም የሚነሳሰበት ወቅት ነው፡፡ አዲስ አመት ሲመጣ መንግስት ያቅዳል ፣ በአዲሱ አመት ይህንን እጀምራለሁ ፣ ያንን አጠናቅቃለሁ ይላል፡፡ ለምሳሌ እንደ ንግድ ሚንስቴር፣ እንደ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የመሳሰሉ ከወጭ ንግድ ጋር የተያየዙ ስራዎችን የሚሰሩ ተቋማት በአዲሱ ዓመት (በበጀት አመቱ ማለታችን መሆኑን ልብ ይሏል)፡፡ ሌሎችም ከመንግስትና ከተቋማት ባሻገር እንዲሁ የግል ኩባንያ ደረጃ እና በግለሰብ ደረጃ ያሉትም እቅዳቸውን አስቀምጠው ለማሳካት በአዲስ ጉልበት ለመንቀሳቀስ የሚያከብኩብበት ነው አዲስ አመት፡፡

እቅድ ማውጣት ከሕይወት የሆነ ነገር እንድንጠብቅ ያደርገናል፡፡ ሰዎች ምኞቶች እና ህልሞች ካሏቸው ደግሞ ይበልጥ የተሻለ ቦታ ለመድረስ ይፈልጋሉ፤ ይጥራሉም፡፡ አዲስ ዓመት አዲስ ተስፋ የሚሰነቅበት፣ በኑሮ ላይም አዎንታዊ ለውጥን ለማድረግ ዕቅድ ይዘን የምንነሳበትም ነው፡፡ በአዲስ ዘመን ሀገርና ህዝብ በአዲስ መንፈስ፣ በአዲስ ዕቅድና በአዲስ ተስፋ መጪውን ዘመን ይቀበሉታል፤ ከአሮጌው ዘመን በመማር ለአዲሱ አመት የተለያዩ ዕቅዶችን ያወጣሉ፡፡ መልካም ነገሮችን ይዘው ይነሳሉ፡፡

ዕቅድ ማለት ሰዎች በአዲስ አመት የተሻሉ ለመሆን ለራሳቸው የሚገቡት ቃል ጭምር ነው፡፡ እንዲሁም የአዲስ አመት ዕቅድ አንድ ሰው አንድ ጥሩ ነገር ለመሥራት ወይም መጥፎ ባህሪን ለማራቅ ለራሱ የሚገባው ቃልም ነው፡፡ በተለይ ወደ ንግድ ስራ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ነጋዴዎች ስኬታማ ቢዝነስን ለመመስረት፣ ዕቅድ የሚይዙበት ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ እቅድ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነው ይህውም ህይወትን መልካም እና የተሻለ ለማድረግ ነውና ለሰዎችም መልካም ሆኖ መገኘትንም መዘንጋት አይኖርበትም፡፡

አዲሱ ዓመትን ስናወሳ አሮጌውን አመት አበቃ ደቀቀ ብሎ መርሳት አያስፍልግም፡፡ ምክንያት ወደኋላ ዘወር ብሎ ያሳለፍነውን በመፈተሽ የተከወነውን ለማድነቅ በዕቅድ ብቻ የቀረውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ይበጃልና፡፡ አዲስ አመትና እቅድ የአንድ ሳንትም ሁለት ገፅታዎች እንደሆኑ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ከግለሰብ አንስቶ እስከ ሀገራዊ እቅዶች በሁለት መሰረታዊ ችግሮች ከግብ ሳይደርሱ በወረቀት ላይ ብቻ በእቅድ ላይ እንደሚቀሩ አመላክቷል፡፡ የመጀመሪያው እቅዱን ለማሳካት የሚረዱ ምቹ ሁኔታዎችን የመለየት ውስንነት ሲሆን ይህም የራስ አቅምንና ከእቅዱ መጠን ጋር ያለማጣጣም ችግር ነው፡፡

እቅድ እንዳይሳካ ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን መለየት ተገቢ መሆኑን ያስፈልጋል፡፡ በተግባራ ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች ቀድሞ የእቅዱን አካል ማድረግ ከተቻለ ግን በቀላሉ ማለፍ ይቻላል፡፡ አለማቀድ አለመቻል ፣ ለመውደቅ ማቀድ ነው ይላሉ ነጮች፡፡ ከዚህ አንፃር ሳያቅዱ ውጤታማ ከመሆን አቅዶ ውጤት አልባ መሆን ይሻላል፡፡ ምክንያቱም እንደ ሎተሪ ድንገት የመጣ ስኬት ወይንም እድገት በእቅድ የማይመራ ከሆነ የትም መድረስ አይችልም፡፡

እቅድ መሆን ያለበት በበጀት መጠን ሳይሆን በመስራት አቅም ልክ ነው ሲሉ ሙህራን ይናገራሉ፡፡ በርግጥ እቅዱን ለማሳካት ገንዘብ እንደሚያስፈልግ ግልጽ ቢሆንም ባዶ እጄን ነኝ ብሎ ከማቀድ መታቀብ ግን ተገቢ አይደለም ይላሉ፡፡ ታዲያ! እቅዳችን የሥራ ፣ ንግድን የማስፋፋት ወይንም አዲስ የመጀመር ፣ የትምህርት ፣ የትዳር ፣ የመውለድ ፣ ሌላም ሌላም ሊሆን ይችላል፡፡ ምኞታችንም የማደግ የመለወጥ ሊሆን ይችላል፡፡ እቅድን በማሳካት ካሰብነው ግብ ለመድረስ ግን በቅድሚያ የአካልና የስነ ልቦና ዝግጅት ይጠይቃል፡፡

የዘመኑ መቀየር ከቁጥር በዘለለ በእኛ ህይወት ውስጥ የተለየ ቦታ አለው፡፡ ሌላው ስለአዲስ ዓመት ስንናገር የሰው ልጅ በአዲስ አመት የተሻለ ደረጃ ለመድረስ ያቅዳል፣ ያስባል፡፡ የአዲስ አመት ዕቅድ ማለት ሰዎች በአዲስ አመት የተሻሉ ለመሆን ለራሳቸው የሚገቡት ቃል ነው፡፡ እቅድ ብቻ ግን ከግብ አያደርስም፡፡ አዲስ ዓመትን አስታኮም ሆነ ሳይሆን የምናወጣቸው እቅዶች እንዲሳኩ በርካታ ከግምት ውስጥ የምናስገባቸው ነገሮች አሉ፡፡ ባለሙያዎች እቅድ ከማውጣታችን በፊት ጥሩ አድርገን ራሳችንን ማበረታታት እና ማነቃቃት ያስፈልጋል» ይላሉ፡፡

ጥሩ እና መጥፎ ጎኑን መለየት፣ ብዙ ነገሮች ሳይሆን ዋና ዋና የሚባሉ ነገሮችን መምረጥ እና ዲሲፕሊን ወሳኝ ናቸው ይላሉ፡፡ ሌላው ግባችንን ለማሳካት ልማድ ልናደርገው የሚገባን ነገር ፣ ባለሙያዎች እንደሚሉት እቅዳችንን በጽሑፍ ስናስቀምጥ ነው፡፡ እቅድ የግድ አዲስ ዓመትን አስታኮ መሆን ባይኖርበትም ከአዲስ ዓመት ጋር ማገናኘቱ ጥሩ ነው ይላሉ፡፡ « የተለመደ ነገር ነው ነገር ግን ሌላም ጊዜም እቅድ ማውጣት ይቻላል፡፡ አይምሮዋችን መለወጥ አለበት ብሎ በተነቃቃ ጊዜም እቅድ ማውጣት ይኖርብናል፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ የተወሰኑ ሀገራት አዲስ ዓመትን የሚያከብሩበት ዕለት ከተቀረው የዓለማችን ክፍል የተለየ ነው፡፡ በሁሉም ሀገራት ግን አንድ በጋራ የሚደረግ ነገር አለ፡፡ በአዲስ አመት አዲስ እቅድ ማውጣት! ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አመት በመስከረም ወር ሲከበር፤ ቻይናውያን ለምሳሌ በጥር ወር አጋማሽ ፣ ታይላንዳዊያን ደግሞ በሚያዚያ ወር አዲስ ዓመትን ያከብራሉ፡፡ ሁሉም ጋር ዓመት ምህረቱ እና አከባበሩም ይለያያል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ አዲስ ዓመት አዲስ እቅድም የሚወጣበት ነው፡፡ እቅድ ማውጣት ከሕይወት የሆነ ነገር እንድንጠብቅ ያደርገናል፡፡ ሰዎች ምኞቶች እና ህልሞች ካሏቸው ደግሞ ይበልጥ የተሻለ ቦታ ለመድረስ ይፈልጋሉ፤ ይጥራሉም ይላሉ ባለሞያዎች፡፡ በዚያው በተሰጠው ዘመን ሁሉም ሥራውን ያከናውናል፡፡ አከናውኖም ያልፋል፡፡ ስለ አዲሱ ዓመት ሲነሳ አሮጌውን አመት መዘንጋት አይገባም፡፡ ምክንያት ወደኋላ ዘወር ብሎ ያሳለፍነውን በመፈተሽ የተከወነውን ለማድነቅ በዕቅድ ብቻ የቀረውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ይበጃልና፡፡ ስኬት የራቀው ከብርታቱ በመለየቱ ተጸጽቶ ወደፊት ጠንክሮ ለመሥራት ታጥቆ ለመነሣት፣ ክፉ ሥራ ሠርቶ ፈጣሪን ያስቀየመ ቢኖር ንስሐ ገብቶ ወደ ፈጣሪው ቀርቦ ለመዘጋጀት፣ በሌሎች መበለጥ ተሸፍኖ የቆየ በመብለጥ ጎዳና ላይ ለመረማመድ የሚያስችል መንፈሳዊ ቅናት ቢያድርበት፣ የዘመን መለወጥን ያህል ልዩ አጋጣሚ አይገኝም፡፡ ዘመን የሰው ልጆች ስራቸውን በጊዜ እያለኩ ወደ ውጤት ለማምጣት ካልሆነም በመጪው ለማሻሻል ቃል የሚገቡበት ከፈጣሪ የተሰጠ ፀጋ ነው፡፡ ስለዚህ ይሆን ዘመን ታዛዥ እንጂ አዛዥ አይደለም የሚባለው፡፡ አዲስ ዓመት በየዓመቱ የሚሰጠን ዕድል የትናንት ስህተታችንን

**ወደ ገጽ 6 የዞረ**

# አዲስ አመትና እቅድ!...

ከ ገጽ 5 የዞረ

እንድናርም፣ በጎ በጎውን እንድናስብ ብሎም እንድንፈፅም ነው። የዘመኑ መቀየር ከቁጥር በዘለለ በእኛ ህይወት ውስጥ የተለየ ቦታ አለው። ሌላው ስለአዲስ ዓመት ስንናገር የሰው ልጅ በአዲስ አመት የተሻለ ደረጃ ለመድረስ ያቅዳል፣ ያስባል። የአዲስ አመት ዕቅድ ማለት ሰዎች በአዲስ አመት የተሻሉ ለመሆን ለራሳቸው የሚገቡት ቃል ነው። የአዲስ አመት ዕቅድ አንድ ሰው አንድ ጥሩ ነገር ለመሥራት ወይም መጥፎ ባህሪን ለማረቅ ለራሱ የሚገባው ቃልም ነው። በተለይ ወደ ንግድ ስራ የሚቀላቀሉ አዳዲስ ነጋዴዎች በአዲሱ አመት ስኬታማ ቢዝነስን ለመመስረት፣ ዕቅድ የሚይዙበት ነው። ዞሮ ዞሮ እቅድ ለሰው ልጅ አስፈላጊ ነው ይህውም ህይወቱን መልካም እና የተሻለ ለማድረግ ነውና ለሰዎችም መልካም ሆኖ መገኘትንም መዘንጋት አይኖርበትም። የአዲስ አመት ዕቅዶች ብዙውን ጊዜ በተለያየ ሁኔታ ሊታቀዱ ይችላሉ።

ሌሎች ሰዎች ደግሞ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መርሃ ግብር ለመጀመር፣ የሥራ ዘርፍን ለመቀየር ወይም ማህበረሰብን በበጎ ፈቃደኝነት ለማገልገል እና መልካም ልምድን ለማዳበር ቃል ይገባሉ። ብዙ ሰዎች አዲስ ዓመት ሲመጣ አዲስ ቢዝነስ ለመጀመር ፣ የጀመሩትንም ቢዝነስ ሰለማስፋፋት ፣ ከሱስ ለመውጣት፣ አዲስ ህይወት ሰለመጀመርና ሕይወታቸውን ለመቀየር ይወጥናሉ፤ ያቅዳሉ። ችግሩ ቃል የመግባት ሳይሆን ቃልን አክብሮ ራስን መለወጥ ላይ የሚታዩ ችልተኝነቶች የሚያመጧቸው አሉታዊ ውጤቶች ናቸው።

ስለሆነም የአዲስ አመት ዕቅድን ወደ ተግባር ለመለወጥ መጣር እና ለቃላችን መታመን ደግሞ ከእኛ ይጠበቃል። ብዙዎቻችን ህይወታችንን ለመለወጥ ወደ አዲስ ዓመት እንገባለን፣ ነገር ግን ከዓመት ወደ ዓመት ምንም የተለወጠ ነገር አናገኝም። አንዳንድ ሰዎች በአዲስ ዓመት የተሻሉ ለመሆን ወይም ለመለወጥ ቃል ይገባሉ። ግን ፣ በመስከረም ወር ከታቀደው ዕቅድ ውስጥ የተወሰነው የሚሆነው በጥቅምት ወር ሳይሳካ ይቀራል። ለአዲሱ ዓመት ያቀዷቸው እቅዶች ካልሰሩ ወይም ካልተሳኩ ወደ ዕቅድ ሰሌዳው መመለስ ሊኖርብዎ ይችላል። ይህ ማለት የእርስዎ ዕቅድ ወይም ዘዴ አይሠራም ማለት ነው፤ ስለዚህ የተዘጋጀውን እቅድ እንደገና በመፈተሽ ለችግሩ አዲስ መፍትሄ ማዘጋጀት ይኖርብናል ማለት ነው። ስለዚህ ስንቶቻችን ነን በአዲስ አመት የተሻለ ለመሆን የተዘጋጀነው? ባለስልጣኑም ህዝቡን ለማገልገል፣ የህግ ባለሙያውም ሚዛናዊ ፍርድ ለመስጠት፣ ነጋዴውም ነግዶ ለማትረፍና ደንበኞችን ለማፍራት ፣ በአዲስ አመት ይዘጋጃል። እያንዳንዱ አዲስ ዓመት ቅዱስ በረከቶችን ያመጣልና የመልካሚ ኢትዮጲያ ልጆች ኑ የተሻለ ዘመን እንፍጠር። **መልካም አዲስ አመት!!**

# በገቢዎች ቢሮ ባለው ብልሹ አሰራርና ሙሰና እየተማረሩ መሆናቸውን በጋራዥና ማምረቻ ዘርፍ ላይ የተሰማሩ የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ገለፁ

**በከፍያለው ዋሲሁን**

የዘርፍ አንቀሳቃሾች ይህንን የገለፁት የአዲስ አበባ ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ጋር በመተባባር በተዘጋጀ የኤሌክትሮኒክስ ታክስ እና የግብር ሰርዓቱ በተመለከተ ግንዛቤ መፍጠሪያ መርሃ ግብር ላይ ነው። የአዲስ አበባ ከተማ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አድም ኑር ከግብር ከፋዩ ህብረተሰብ ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ግንዛቤ ማሰጨበጥ የተቋማቸው አንዱ ሀላፊነት ነው ብለዋል።

አክለውም አሁን ላይ መንግስታቸው የግብር ሰርዓቱን ዲጅታል ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የከተማዋ የልማት ፍላጎት እያደገ የገቢ መሰብሰብ አቅምም በዚያው ልክ እየጨመረ ቢመጣም መሰብሰብ ላይ የሚቀሩ ነገሮች እንዳሉ ገልፀዋል።

በተለይ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች በተመለከተ ግብራቸውን በኤሌክትሮኒክስ መንገድ እንዲያሳውቁና እንዲከፍሉ ስልጠና ከተሰጣቸው 570 ኩባንያዎች መካከል 350ዎቹ ወደ ኢ -ታክስ መግባታቸውንም ገልፀዋል። ሰለ ኢ-ታክስና የግብር አከፋፈል ሰርዓቱ ምንነት በተመለከተ ገለፃ ያደረጉት የቢሮው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ዳሬክተር አቶ አብዱል አዚዝ --- ባደረጉት ገለፃ የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን በኢ -ታክስ አማካኝነት እንዲከፍሉ ጅማሬዎች አሉ ብለዋል።

ይህ አሰራር የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ባሉበት ቦታ ሆነው ጊዜና ጉል በታቸውን ሳያባክኑ እንዲከፍሉ መደረጉ ከፍተኛ አበርክቶ አለው ብለዋል።

አሰራሩ በ2013 ሲጀመር ግብራቸውን በኤሌክትሮኒክስ መንገድ ያሳወቁና የከፍሉ የንግድ ማህበረሰብ አባላት ቁጥር 41 እንደነበር አስታውሰው።

አሁን ላይ ቁጥሩ ከአመት አመት እያደገ በመሄድ ላይ ይገኛል ብለዋል። ለአብነት እስከ ነሀሴ 16 ቀን 2015 ድረስ በነበረው ጊዜ 325ሺ የሚሆኑ ነገዴዎች ግብራቸውን በኢ ታክስ አማካኝነት ያሳወቁ ሲሆን በዚህም ከ3 ነጥብ 1 ቢሊየን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን አስታውቀዋል።

በግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ የተገኙት የዘርፍ ምክር ቤት አባላቱ ከግብር አከፋፋል ጋር አሉ ያሉትን ችግር አንስተዋል።

በጋራዥ ዘርፍ ላይ እንደተሰማሩ የገለፁት የምክር ቤቱ አባል ‹‹ቴክኖሎጅ መልካም ነገርና ከወረፋ የሚገላግል በመሆኑን ›› ለግብር ከፋዩም ሆነ ሰብሳቢው መልካም ነው ብለዋል።

አያይዘውም አሁን ላይ እንደ ችግር ሆኖብናል ያሉት የባንክ ተቀማጭና ካፒታል ላይ ግብር እየተጣለብን ነው ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

‹‹ኢ ታክስ በ2013 ነው የጀመርኩት›› ያሉት ሌላኛው ተሳታፊ በበኩላቸው በተለይ ‹ቫት› ተመላሽ ሰንጠይቅ አንቀበልም እየተባልን ነው ይህ ለምን ሆነ ሲሉ ጠይቀዋል።

አያይዘውም ካፒታል ስናሳድግ በልዩነቱ ላይ ግብር እንድንከፍል እየተደረግን ነው ሲሉ ገልፀዋል።

በቢሮው ቅርንጫፍ መሰሪያ ቤት ሰራተኞች ፤ ልክ አይደለም በማለት ይሄን ያህል ክፍልና ይቀነስልህ የሚል ድርድር ውስጥ እንድነገባ እየተገደድን ነው ብለዋል።

የማምረቻው ኢንዱስትሪ በመንግስት ልዩ ትኩረት ቢሰጠውም ገቢዎች ላይ ግን ያንን ከግምት ውስጥ ያስገባ አሰራር የለም ብለዋል ተሳታፊዎች።

የከተማ አስተዳደሩ ገቢዎች ቢሮ የታክስ ዘርፍ ም/ ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘገየ በላይነህ ባንክ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ታክስ እንድንከፍል እየተደረገ ነው በሚል ለተነሳው ጥያቄ ይህ ልክ አይደለም ፤ ከተፈፀመም እርማት እንወሳደለን ብለዋል።

ነገር ግን ገንዘቡ ከየት መጣ የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት ያሉት አቶ ዘገየ ‹‹ለምሳሌ ድርጅቱ 500 ሺ ብር ቢሆንና ወጭው 400ሺ ብር ሆኖ ትርፉ አንድ መቶ ሺ ብር ቢሆን የሚከፍለው 35ሺ ብር ብቻ መሆኑን ገልፀዋል።ሆኖም ገንዘቡ 10 ሚሊየን ብር ከሆነ ገንዘቡ ከየት መጣ የሚለውን ማጣራት ያስፈልጋል ብለዋል።

መመሪያ ቁጥር 176 /2014 መሰረት ሂሳብ ላይ ለገባ ገንዘብ የማሳየት ኃላፊነት የባለ ገንዘቡ መሆኑን እንደሚደነገግግ ም/ ል ቢሮ ኃላፊው ተናግረዋል።

አክለውም ካፒታል ሰናሳድግ ታክስ እንደሚደረግ ጠቅሰው ካፒታል አሳድጋለሁ ካለ ምንጬ መታወቅ አለበት።

ካፒታሉን ሲያሳድግ ምንጬ ምንድን ነው ከትርፍ ነው ተበድሮ ነው ወይ የሚለው መመለስ አለበት ብለዋል። አቶ አብዱላዚዝ ...በኢ-ታክስ አተገባበበር ላይ መልካም የሚባሉ ጅምሮች ቢኖሩም አሁንም ሊፈቱ የሚገባቸው ችግሮች እንዳሉ ገልፀዋል።

በተወሰኑ የንግድ ማህበረሰብ አባላት ዘንድ ያለውን የአሰራር ለውጥ ያለመቀበልና በተለምዳዊው አሰራር መንገድ መቀጠል መፍለግ አንዱ መሆኑን አንሰተዋል።

ትክክለኛ የግብር ከፋዩን ስልክ አለማስገባት ፤ ሰልክ ቁጥርን በተደጋጋሚ መቀየር እና የኔት ወርክ ችግር ፈተና ኢ-ታክስን ለመተግበር ፈተና እንደሆነበት ገልፀዋል።

የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት አቶ ፋሲካው ሲሳይ በተጠናቀቀው አመት የንግዱ ማህበረሰብ በአራት ጉዳዮች ዙሪያ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት መደረጉን አንስተዋል።

የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ በተያዘው 2016 በጀት አመት 140 ቢሊየን ብር ለመሰብሰብ እቅድ መያዙን ሰምተናል።

# አማራጩ የብሪክስ ገበያ




**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

ኢትዮጵያ የዓለምን ንግድ ሥርዓት ቀድመው ከተቀላቀሉ ጥንታዊ አገራት አንዷ እንደነበረች ታሪከ ይነግረናል፡፡ ከ5ሺ 5 መቶ ዘመን በላይ ባስቆጠረው የዓለማቀፍ ግንኙነት ረዥም ታሪክ ውስጥ ንግድ የአገራት የግንኙታቸው ዋናው ሃዲድ ነው፡፡ አገራት የንግድ ግንኙነት የሚመሰርቱት ጓዳቸውን እያዩ እና የሌላውን ትሩፋት እያማተሩ ሲሆን ግንኙነታቸው በየጊዜው ተለዋዋጭ እና ከአንዱ የገበያ ቀጣና ወደ ሌላው የሚቀያየሩበት ነው፡፡ ዛሬ ላይ የአገራት ንግድ ግንኙነት እንደ አንድ የሉላዊነት ምልክት እየሆነ መጥቷል፡፡ በተለይ የመረጃ ቴክኖሎጂ በፍጥነት መስፋፋትን ተከትሎ አንድ ሸቀጥ ከአንዷት የገጠር ቀበሌ ተመርቶ በደቂቃዎች ልዩነት የዓለም ገበያ ላይ ይውላል፡፡




አውሮጳ እና ሰሜን አሜሪካ ያሉ አገራት ሸቀጥ፤ቴክኖሎጂ እና መድሐኒት ወዘተ ይዘው ለገበያ ሲቀርቡ አፍሪቃ ደግሞ በአብዛኛው ልጆቿን በመሸጥ ነበር፡፡ አህጉራችን አፍሪካ ወደ አለም ንግድ እንዴት ተቀላቀለች ብለን ስንመረምር የአፍሪቃ አገባብ የተለየ ነበር፡፡ ይህም በታሪክ አስነዋሪው የባርያ ንግድ በደራበት ዘመን አፍሪቃ ልጆቿን በባርነት ከባሕር ማዶ በመሸጥ ነበር ይላሉ የታሪክ ተመራማሪዎች፡፡ እንግዲህ አንዲህ አንዲያ እያለ የቀጠለው የዓለም ንግድ ሥርዓት በአመታት ታሪኩ ውስጥ አፍሪቃን የአንድ እጅ ጣቶች ቁጥር የማይበልጡ ጥቂት ሃብታም በሚዘወር ንግድ ሥርዓት ውስጥ የቆየች እና በዓለም ንግድ ውስጥ አፍሪቃ በአመዛኙ የበይ ተመልካች ሆና ቆይታለች ማለት ይቻላል፡፡

የዓለም ንግድና የኢኮኖሚ ግንኙነት አዋቂዎች እንደሚሉት በተለይ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ አመታት ላይ የተቋቋሙት የዓለም ባንክ እና የዓለም ገንዘብ ድርጅት የተባሉት ተቋማት ጥቂት ሃብታም አገራት ብቅ አሉ፡፡ ያኔ እነዚህ ሁለቱ የገንዘብ ተቋማት አገራት የሚገጥማቸውን የልማት እና የበጀት ጉድለቶች እየሞሉ አገራትን ከቀውስ ይታደጋሉ በሚል የዓለምን ኢኮኖሚ ማሕራዊ ዕደገትን ያፋጥናሉ ተብለው በብዙ ተስፋ ተጥሎባቸው ነበር፡፡ እየዋለ እያደር ግን ከባንኩም ይሁን ከገንዘብ አበዳሪ ድርጅቱ የተበደሩ አገራት አንኳን የተበደሩትን ሊመልሱ ቀርቶ ከአመት አመት ዕዳ እየተቆለለባቸው ፍዳቸውን ሲያዩ ቆይተዋል፡፡ የአፍሪቃ አገራትን ጨምሮ ሌሎቹ ታዳጊዎች አሁን አሁን ላይ ከሚስተዋለው የዓለም ኢኮኖሚያዊ እና የፖለቲካ ውጥንቅጥ በተለይም የሩሲያና የዩክሬን ግጭት በአገራት መካከል የአሰላለፍ ለውጥ ከማሳየት አልፎ በዓለም የንግድና ኢኮኖሚ ሥርዓት ላይ የራሱን ጥላ ያጠላ ይመስላል፡፡

አዲሱ ማሕበር በእንግሊዝኛው ምዕጻር 'ብሪክስ' የተባለው በሩሲያ፤ብራዚል፤ቻይና ሕንድና ደቡብ አፍሪቃ የመሰረቱት ማሕበር ሲሆን ሰያሜውም የየአገራቱን ስም የመጀመሪያ የእንግሊዝኛ ፊደል በመውሰድ የተመሰረተ ነው፡፡፡

እ.ኤ.አ. በ2006 የተመሠረተው ብሪክስ ከአራት ዓመታት በኋላ ደቡብ አፍሪካን በማከል የአምስት አገሮች ማኅበር ለመሆን በቃ፡፡ ማኅበሩ ዛሬ የዓለምን ጥቅል ምርት (ጂዲፒ) 1/3ኛ የሚሸፍኑና የዓለምን 3.2 ቢሊዮን ሕዝብ የያዙ አገሮች ስብስብ ነው፡፡ ወደ እዚህ የኢኮኖሚ ማኅበር እንደ ኢራን፣ ሳዑዲ ዓረብያ ፣ የተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ እና ኢንዶኔዥያ የመሳሰሉት አገራት ለመግባት ፍላጎት ማሳየታቸው ማሕበሩን ወደ አንድ አዲስ እና ግዙፍ የኢኮኖሚ ቀጣና ይቀይረዋል፡፡

በእስያ አገራት ኢኮኖሚ ተመራማሪ የሆኑት እና በቅርቡ 'Can BRICS DeDolaraze the Global Finacial System' የተሰኘ መጽሐፍ ያሳተሙት ዞዊ ፡ ሊዩ ሁን እንደሚሉት ብሪክስ በታዳጊ አገራት ሰፊ ዕድል ይዞ የመጣ ነው ይላሉ፡፡

ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አንጻር ስመለከተው እንደ ሳዑዲት አረብያ፤የተባበሩት የአረብ ኢምሬቶች፤ኢራን፤ኢትዮጵያ የመሳሰሉት አገራት መጨመር ብሪክስን በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማሳረፍ የሚችል እንደሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ይህ ማሕበር የዓለምን ሲሶ የአጠቃላይ ምርት ያመነጫል ፤ የዓለም 1/4ኛ ወጪ ንግድ የሚጫነው ከብሪክስ አባለት ነው፤ የዓለም ግማሽ ገደማ የሚሆነው ሕዝን ያለው እዚሁ ነው፡፡ የዓለም ግማሹ ነዳጅ የሚቀዳው ከብሪክስ ክልል ነው፡፡ ቻይና እና ሕንድ ደግሞ እጅግ ፈጣን የሆነ እድገት እያመጡ ነው፡፡ታዲያ ይህን ሁሉ ሃብት በእጃቸው ያደረጉት የብሪክስ አባላት አንዴት በዓለም ንግድና ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ሚና ለመጫወት ምን ይከለክላቸዋል ? ሲሉ ይሞግታሉ፡፡

የሆነው ሆኖ የብሪክስ አባላት ባሳለፍነው ዓመት መጨረሻ 6ኛው ጉባዔውን በደቡብ አፍረቃ አካሂደዋል፡፡ ጉባዔውም ዋነኛው የአለም ትኩረት ሆኖ ሰንብቷል፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ ጉባዔ አገራችን አባል መሆኗም ጭምር ተሰምቷል፡፡ በተለይም እንደ ኢትዮጳያ ያሉ ለማድግ ለሚውተረተሩ አገራት ማሕበሩ እንደ አንድ አማራጭ የኢኮኖሚ ዕድል ይታያል፡፡

አገራችን ከሁሉም የማሕበሩ አባል አገራት ጋር መልካም የሚባል ንግድ ግንኙነት አለት፡፡ ምዕራባውያን በሩሲያ ላይ በጣሉት ማዕቀብ ሳቢያ ከሩሲያ ጋር ለመገበያየት ችግር ለገጠማቸው እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገራት የውጪ ንግዳቸውን ለማሳደግ የብሪክስ መፈጠር ምልካም ዜና ነው፡፡ በመጪው አዲሱ የፈረንጆች አመት በይፋ አባልነታቸው ከሚታወጅላቸው አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ የብሪክስ ማሕበር ሳይታሰብ የተገኘ አማራጭ የገበያ ዕድል ነው ሲሉ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡

የብሪክስ ማኅበር ማደግና መፈጠርም ለምዕራባውያኑ ከባድ ፈተና እንደሆነ ይነገራል፡፡ እ.ኤ.አ. ከ1944 ጀምሮ እንደ ‹‹አይኤምኤፍ›› እና ‹‹የዓለም

ወደ ገጽ 8 የዞረ

# አማራጩ የብሪክስ ገበያ...

ከ ገጽ 7 የዞረ



ባንክ›› ያሉ ተቋማትን በመገንባት ዓለም አቀፍ ተፅዕኖውን አፈርጥሞ የቆየው የምዕራቡ ዓለም ዛሬ ላይ ከባድ ተገዳዳሪ መጥቶበታል። የብሪክስ ማኅበር የፈጠረው ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ (New Development Bank) አዲሱ የዓለም ሚዛን አስጠባቂ እየተባለ ይገኛል።

ዘመዴነህ ንጋቱ የፌርፋክስ አፍሪቃ ፈንድ ሊ/መንበር በበኩላቸው ኢትዮጵያ በፈጣን የኢኮኖሚ አዕድገት ላይ የምትገኝ አገር ናት። ከሠሐራ በታች ካሉት አገራት ናይጀሪያ ለጥቃ ሁለተኛ ትልቅ ኢኮኖሚ ለመሆን ችላለች፡፡ የጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርቷ 156 ቢሊየን ዶላር ደርሷል።

የዛሬ 20 እና 25 አመት ገደማ ቢበዛ ከ8 ቢሊዮን ዶላር አይበልጥም ነበር። ብሪክስ አባላትን ስንመለከት ፈጣን ዕድገት ለማምጣት የሚሮጡ አገራትን ይመርጣሉ። ሌላው ደግሞ የቡድን 7 የተባለውን የሃብታም አገራትን ተጽዕኖ አማራጭ ሆኖ ለታዳጊ አገራት መገኘቱ ነው። ስለዚህ ከኢትዮጵያ አንጻር ስንመለከት የብሪክስን አስፈላጊነትን መገመት ይቻላል። ኢትዮጵያ በርካታ ህዝብ ያላት ስትሆን አብዛኛው ደግሞ ወጣት ነው። ዛሬ ላይ ወደ 127 ሚሊየን የሚጠጋ ሕዝብ ያላት የወጣቶች አገር መሆኗ በራሱ ከአባል አገራቱ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንድታገኝ ይረዳል። በተለይም በብዛት የሰው ሃይል የሚፈልጉ ትልልቅ ኢንዱስትሪዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲያማትሩ ያደርጋቸዋል።

ሌላው የብሪክስ መመሥረት ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የአፍሪቃ አገራት ከምዕራባውያኑ የፋይናንስ ተቋማት እና ዓለማቀፍ ድርጅቶች ተጽዕኖ ተላቅቀው አፍሪቃውያን ድምጻቸውን የሚያሰሙበት እና የራሳቸውን የልማት ስተራቴጂ እንዲተገብሩ ያስችላቸዋል። የልማት ብድር ለማግኘት ከአለም ባንክ እና የዓለም ገንዘብ ድርጅት አስጨናቂ ቅድመ ሆኔታዎች በብሪክስ ቤት የሉም፡፡ ኢትዮጳያ በቀላሉ ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በቀላሉ የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት ትችላለች። ስለዚህ ለኢትዮጵያ ብሪክስ ብዙ ትሩፋት አለው እላለሁ። ሁኔታዎች በጥሩ ከቀጠሉ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት 20 እና 30 ዓት ውስጥ ትልቅ እድገት ላይ ትደርሳለች ብየ አምናለሁ።

ዕውቁ የምጣኔ ሃብት ተመራማሪ ዶ/ር ቆስጠንጢኖስ በርሔ ነገሩ ያዋጣናል ወይ ተብለው በአንድ የብዙሃን መገናኛ በሰጡት ማብራሪያ ‹የእኛ የብሪክስ አባል መሆን ብዙ ዓይነት ጠቀሜታ አለው። የብሪክስ አባል አገሮች ከፍተኛ የልማት ሀብት ያላቸው ናቸው። የብሪክስ ባንክ ራሱን የቻለ ብዙ ብድር ሊገኝበት የሚችል ነው ይላሉ። ይኸው የብሪክ ባንክ ከ2016 እስከ 2022 ባሉት 5 አመታት ውስጥ ወደ 123 የሚሆኑ የልማት ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ አድርጓል። በየአመቱ እያንዳንዱ አባል አገር በፕሬዝደንትነት ለአንድ አመት የሚመራው ብሪክስ ከአሁኑ በብዙ አገራት ዘንድ ተስፋ የፈነጠቀ ይመስላል። በተለይም ለወጪ ንግድ መዳረሳችን መስፋፋት እና በአባልነት ከሚገኙ ልዩ መብቶች የአገራችን የንግድ ሕብረተሰብ በስፋት ተሳታፊ እንደሚሆን ይታሰባል።

ባለ ነዳጅ የአለማችን ሀገራትን ጨምሮ በርካታ ሀገራት ብሪክስን ለመቀላቀል ጥያቄ ማቅረባቸው ይታወሳል። ይህም የብሪክስን መጻዒ ቀናት በተስፋ እንዲታጀብ እድርጓል ሲሉ የዘርፉ አዋቂዎች ይናገራሉ።



# አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት

ADDIS ABABA CHAMBER OF COMMERCE AND SECTORIAL ASSOCIATIONS

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

አዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 17ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን በአዲሱ ኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ሐሙስ ከቀኑ 7:30 ሰዓት ጀምሮ ያካሂዳል፡፡ ጉባኤው የ2015 በጀት ዓመት የሥራ ክንውንን ይገመግማል፡፡ የውጭ ኦዲተሮች የሚያቀርቡትን ሪፖርት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

በመሆኑም በዚህ ለምክር ቤታችን የወደፊት እርምጃ እጅግ ወሳኝ በሆነ ጉባኤ ላይ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ሐሙስ ከቀኑ 7:30 ሰዓት ጀምሮ በኢንተርላግዥሪ ሆቴል ተገኝተው እንዲሳተፉ የአክብሮት ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ቢሆን፣ ለዚሁ የተዘጋጀውን የውክልና ደብዳቤ የያዙ የድርጅትዎን ባልደረባ መላክ የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ይቻላል
It's Possible!

ንግድ ምክር ቤት ህንፃ ሚክሲኮ አደባባይ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Chamber of Commerce Building Mexico Sq. Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ/Tel: +251 115 518055 ፋክስ/Fax: +251 115 511479
P.O.Box 2458 አዲስ አበባ፣ ኢትዩጵያ/Addis Ababa Ethiopia ኢ ሜይል/E-mail: Infor@addischamber.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# ከሥደት ተመላሿ ሥራ ፈጣሪ



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በወጣትነት ዕድሜ ብዜ የሚሮጥበት፣ ቁጥር ስፍር የሌለው ፍላጎት እና ምኞት የሚፈልቅበት አንዲሁም ረዣዥም ሕልሞች የሚስተናገዱበት የዕድሜ ክልል ነው ቢባል አብዛኞቻችንን ያስማማል:: ወጣትነት እንዲሁ አንዴ የሚነሱበት ሌላ ጊዜ ደግሞ የሚወድቁበት ወራት ነው:: በዓለማችን ላይ ዛሬ አንቱ የተባሉ የኩባንያ ባለቤቶች አንደው እንደዋዛ ዛሬ ካሉበት የተገኙት ትናንት እጅግ ዝቅ ብለው የቆዩ እና ከምናምንቴዎች አንዱ ተብለው የተቆጠሩ ነበሩ::

የስኬታማ የአገራችን ሥራ ፈጣሪዎች መካከል አንደ አቶ በቀለ ሞላ ፣አንደ አቶ ማሞ ካቻ እና ሌሎችም ከውጤት የደረሱት ከአስር አንድ ሁለት ብለው ነው::

አሁን አሁን በተለይ በወጣቶች ዘንድ ከትንሽ ተነስቶ የራስን ሥራ ፈጥሮ ራስን እና ወገኖችን መርዳት እየተለመደ የመጣ ባህል ይመስላል:: በተለይ በሴቶች እህቶቻችን ዘንድ በትንሹ ተነስተው ፈተናን በትዕስት እና በብልሃት አልፈው በሁለት እግራቸው መቆም የቻሉ ጥቂት አይደሉም:: ወጣት ሴት ሥራ ፈጣሪዎች ከሚሳተፉበት የሥራ ፈጠራ ዘርፍ መካከል ጨርቃጨርቅ፣አልባሳት፣ቆዳ ፣ዕደ ጥበብ እና ልብስ ስፌት ሥራዎች ይገኙበታል:: በሌላ በኩል ያገራችን ወጣት ሴቶች ወደ አረብ አገራት በመሄድ የሚገፉት መራር እና የሥቃይ እንጀራ ለብዙዎች ደብዛ መጥፋት፣ዘላቂ የአካል እና አዕምሮ ጉዳት መዳረግ፣ እንዲሁም ምትም አለበት:: ውድ አንባቢያን በዚህ ጽሁፍ ከአረብ አገር ስደት ተነስታ አንድ ሁለት እያለች ዛሬ 10 ለሚጠጉ ወገኖቿ እንጀራ እንዲያገኙ ስለበቃች አንድ ብርቱ ወጣት ጥረት ያተኩራል:: የወጣቷን ከትናንት ይልቅ የነገን በማየት ፈተናዎችን አልፎ ከውጤት መብቃት አንደሚቻል በተጨባጭ ያሳየችውን ጥሩ ተሞክሮ ለሌሎች እህቶቻችን መነቃቃት እንዲጭርባቸው እና እንዲበረታቱ ያግዛል ብለን እናስባለን:: ወ/ት ሠርካለም አስፋው ትባላለች መጀመሪያ እኔ ከስደት ተመላሽ ነኝ ሲጀመር እና ቀጥታ ወደዚህ ሥራ ገባሁ በማለት ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ ሀሳቧን ታካፍላለች:: ይህን ስራ ከጀመርኩ በኂላ የተለያዩ ባህላዊ ቀሚሶችን አሁን የአበሻ ቀሚሶች አዘጋጃለሁኝ ብዙ ትዛዞችን እቀበላለሁ በማለት ትናገራለች ይህች ከስደት ተመላሽ ስራ ፈጣሪ:: ከዛ ያኛውን ሲ ኦ ሲ ተፈትኜ ፊልድ ቀይሬ ይህቺ አንዷን ማሽን ነበረች በዛች ነው የጀመርኩት:: ወ/ት ሠርካለም አስፋው በአንድ የስፌት ማሽን ስራ እንደጀመረች ትናገራለች::

የዘርፉ አዋቂዎች አንደሚሉት በሚቀጥሉት 7 አመታት ውስጥ የጨርቃጨርቅ ዘርፍ በዓለም ገበያ እስከ 8 በመቶ ዕድገት ያሳያል:: በዚህ የተነሳ ገበያው ሁሌም እያደገ በሚሄደው ዘርፍ አገራችን አበረታታች ውጤቶች አሳይታለች:: በተለይ መንግሥት ለአምራች ዘርፉ በሰጠው የፖሊሲ ትኩረት የማምረቻ መሠረተ ልማት ድጋፍ የአገር ውስጥ እና የውጪ ባለሃብቶች እየተሳተፉበት ነው:: ነገር ግን በአገር ውስጥ አንደ ወ/ት ሠርካለም ላሉ የአነስተኛ እኛ መካከለኛ የዘርፉ አንቀሳቃሾች መንግሥት አሁን ከሉበት ከፍ ብለው ነጋዴዎች ስኬታማ አምራች እና ላኪዎች አንዲሆኑ የመንግሥት ድጋፍ ይሻሉ:: የገበያ ትስስር አኔ እስከአሁን ድረስ አላገኘሁም ብየ ነው የማስበው :: ምክንያቱም ባዛር ነበር እስከ አሁን ብዙም አላየሁም በማለት ገበያ የማግኘት ሁኔታ ፈታኝ እንደሆነ ትናገራለች::
በነገራችን ላይ ዛሬ የጨርቃጨርቅ እና ስፌት በዓለማችን ላይ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የሚመረቱት በአነስተኛ እና መካከለኛ ኤንተርፕራይዞች ነው:: በነዚህ ኤንተርፕራይዞች አማካኝነት የሚንቀሳቀሰው የዓለም ገበያ እስከ 1.7 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር የሚታፈስበት ነው:: አንደ ቻይና ፣ሕንድ፣ባግላዴሽና አና ማሌዥያ የመሳሰሉት አገራት ዋነኛ የውጪ ምንዛሬ ምንጫቸው ሆኖ ቆይቷል:: መነሻቸውም አነስተኛ ኤንተርፕራይዞች ናቸው::

ወደ እኛ ስንመለስ ለጨርቃጨርቅ አልባሳት ዘርፉ በሌሎችም ተያያዥ እና በብዙ የግል አንቀሳቃሾች ዘንድ የሚገለጹ ችግሮች አሉበት:: ሰርካለም አሁን ያላትን ቢዝነስ ለማሳደግ የብድር አቅርቦት ሌላው ፈተና እንደሆነ ትናገራለች ስለሆነም ብድር እንዲመቻችላት ትጠይቃለች::

የዛሬዋን አንግዳችንን አንደ ማሳያ አቀረብናት አንጂ በሺህ የሚቆጠሩ አነስተኛ እና መካከለኛ አንቀሳቃሾች ከዛሬ ይልቅ ነገን በብሩሕ ተስፋ ተቀብለው የጀመሩትን ጉዞ በችግር ውስጥ አልፈው ከጫፍ አንደርሳለን ብለው ያስባሉ:: አሁንም ይሄ ጥሩ ጅማሮ የታየበት ታዳጊ ዘርፍ የኂሊት አንዳይሄድ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ አስፈላጊውን የፖሊሲ ድጋፍ በማድረግ ሊታደገው ይገባል አንላለን:: እንግዳችን በመጪው አዲስ አመት አሁን ካለችበት ደረጃ ከፍ ማለት ትፈልጋለች:: የሰራተኞቻን ቁጥር አሁን ካለበት የቁጥር መጠን መጨመር ትፈልጋለች:: ነገር ግን የብድር እና የመሬት አቅርቦት ለሰርካለም የአዲስ አመት እቅድ መሳካት ፈታኝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታል::

# የንግዱ ማህበረሰብ ስለ ቻምበር



**ሰለሞን ግዛው የኤች ኤስ ቲ ዋና ስራ አስፈጻሚ**

በአዲስ ቻምበር የአብሮነትና የምስጋና ክብረ በአል ቀን የኤች ኤስ ቲ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰለሞን ግዛው ስለ ምክር ቤቱ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል:: ላለፉት ሀያ አመታት የአዲስ ቻምበር አባል እንደሆኑ የተናገሩት አቶ ሰለሞን አዲስ ቻምበር ለንግዱ ማህበረሰብ በሚሰጠው አገልግሎት እንደተደነቁ ተናግረዋል:: የአዲስ ቻምበር የአድቮኬሲ አገልግሎት የንግዱን ማህበረሰብ ሀሳቦችን ለሚመለከተው አካል በማካፈል የፖሊሲ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በመወትወት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ አድንቀዋል:: በዚህም የተነሳ አዲስ ቻምበር የግሉ ዘርፍ ጣምራ ድምጽ እንደሆነም ተናግረዋል::

ላለፉት ሀያ አመታት አዲስ ቻምበር በሰው ሀብት ልማትና ስልጠና ዙርያ እያበረከተ ያለውን አስተዋጾ አድንቀዋል:: ከዚህም አንጻር አዲስ ቻምበር የቢዝነስ አገልግሎት የንግዱን ማህበረሰብ እውቀት በመገንባት እያበረከተ ያለውን አስተዋጾ አመስግነዋል:: ከነዚህም መካከል በምክር ቤቱ የሚሰጠው

ወደ ገጽ 10 የዞረ

# የንግዱ ማህበረሰብ ስለ ቻምበር...

**ከ ገጽ 10 የዞረ**

የአዲስ ቻምበር የህግ ምክር አገልግሎት በንግዱ ማህበረሰብ በኩል የሚነሱ የህግ አለመግባባቶችን በመፍታት እያበረከተ ያለውን ሚና አድንቀዋል።

የንግድ ትስስርንና የቢዝነስ ልማት አገልግሎትን በተመለከተ አቶ ሰለሞን ግዛው አዲስ ቻምበር ቁልፍ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ አንስተዋል። የንግዱ ማህበረሰብ የኔ የሚለው ተቋም ያስፈልገዋል ከዚህም አንጻር አዲስ ቻምበር የንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ በመሆን የተሻለ አቅም እንዲኖረው በማድረግ በርካታ ስራዎችን መስራቱን ተናግረዋል። በርግጥ በግለሰብ ነጋዴ ወይም ኩባንያ ደረጃ ተጽእኖ የመፍጠር እድል ጠባብ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን ነገር ግን እንደ ቻምበር አይነት ተቋም በርካታ ነጋዴዎችን ያሰባሰበ ከመሆኑ አንጻር የንግዱን ማህበረሰብ ጥያቄ በቀላሉ እንዲመለስ የማድረግ አቅም እንዳለው ተናግረዋል። ትልልቅም ሆነ ትንንሽ ኢንዱስትሪዎች በተናጠል ድምጻቸው ሊሰማ ስለማይችል እንደ ቻምበር አይነት ተቋማትን በመቀላቀል ችግሮቻቸው እንዲፈቱና ጥያቄዎቻቸው ምላሽ እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው።

የምርምር ስራዎችን በተመለከተ አዲስ ቻምበር ከዚህ አንጻር በርካታ ስራዎችን እንደሰራ አቶ ሰለሞን ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ለአብነትም ያክል ምርምርን በተመለከተ የንግዱ ማህበረሰብ በግለሰብ ደረጃ የማይቻሉ የምርምር ውጤቶችን በቀላሉ እንዲያገኝ እና ግንዛቤው እንዲያድግ የአዲስ ቻምበር ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል። እነዚህ ንግድና ኢኮኖሚ ተኮር የምርምር ውጤቶች የንግዱ ማህበረሰብ ወቅታዊ ሀገራዊና አለማቀፋዊ የንግድ ሁኔታዎች እና አቀጣጫዎች ምን እንደሚመስሉ ዝርዝር መረጃዎችን ይሰጣሉ።

የፖሊሲ ደንቦችና መመሪያዎችን ለንግዱ ህብረተሰብ በቀላሉ በማድረስ የአዲስ ቻምበር ሚና ከፍተኛ እንደሆነ አቶ ሰለሞን ተናግረዋል። የአለም አቀፍ የንግድ ድጋፎች በቀላሉ እንዲገኙ የአዲስ ቻምበር ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል። ከዚህም ባለፈ አዲስ ቻምበር ለንግዱ ማህበረሰብ አለምአቀፍ ገበያን በማመቻቸት እያበረከተ ያለውን ሚና አቶ ሰለሞን አድንቀዋል። ከዚህ ጎን ለጎን የቢዝነስ ለቢዝነስ ውይይቶችን በማመቻቸት የምክር ቤቱን ሚና አድንቀዋል።



**ሀርሽ ኮታሪ የሞሀን ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ**

የሞሀን ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ የሆኑት ሀርሽ ኮታሪ ኩባንያቸው የአዲስ ቻምበር የረጅም ጊዜ አባል እንደሆነና ሶስተኛው ትውልድ የምክር ቤቱ አባል እንሆነ የአብሮነትና የምስጋና ቀን በተከበረበት እለት ተናግረዋል። ቀደም ባሉት አመታት በአያታቸው የተቋቋመው ኩባንያ የንግድ ምክር ቤቱ አባል እንደሆነ ከዛም በኋላ አባታቸው እንደተተኩና አሁን ደግሞ በአቶ ሀርሽ የሚመራው ድርጅት በአባልነቱ እንደቀጠለ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። በመሆኑም ከአዲስ ቻምበር ጋር ያለን ግንኙነት ቤተሰባዊና ጥቅል እንደሆነ ተናግረዋል።

የአዲስ ቻምበር የአብሮነትና ምስጋና ቀን በተከበረበት ወቅት ሀርሽ ኮታሪ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል ሆና በመመረጧ የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክታቸውን በእለቱ አስተላልፈዋል። እንደ ህንድና ኢትዮጵያ የመሳሰሉ ሀገራት የዚህ ቡድን አባል መሆናቸው ሰፊ እድል ይዞላቸው እንደሚመጣም ተናግረዋል።

አዲስ ቻምበር ለንግዱ ህብረተሰብ እያበረከተ ያለውን አስተዋጾ በተመለከተ ሚስተር ሀርሽ ኮታሪ ከአዲስ ቻምበር ጋር የነበራቸውን ገጠመኝ አካፍለዋል። ከዚህ ቀደም በአዲስ ቻምበር አማካኝነት የወሰዱት የፋይናንስ ስልጠና የፋይናንስ እውቀታቸውን እንዳሳደገው ከዚህ ስልጠና በርካታ ጥቅሞችን እንዳገኙ በመግለጽ ምክር ቤቱን አመስግነዋል። እንዲህ አይነት ስልጠናዎች በፋይናንስ ዙርያ ያሉ ውሳኔዎችን ለመወሰን ድጋፍ እንደሰጣቸው በመድረኩ ላይ ተናግረዋል። መሰል ስልጣዎች የኩባንያ ሰራተኞቻቸውን አቅም በማሳደግ እና ምርታማነት እንዲያድግ የኩባንያ እድገት እንዲረጋገጥ የበኩሉን አስተዋጾ እንደሚያደርግ ተናግረዋል። ሀኖም ግን እንዲህ አይነት ወሳኝ ስልጠናዎች በሰፊው መተዋወቅ እንዳለባቸው አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል። ስለሆነም የኩባንያ ስራ አስፈጻሚዎችም ሆኑ ስራ አስኪያጆች እንዲ አይነት ስልጠናዎችን ቢወስዱ መልካም እንደሆነ ሚስተር ሀርሽ ተናግረዋል።

አዲስ ቻምበር የንግዱን ማህበረሰብ በሀገር ውስጥም በውጭም ትስስር እንዲፈጥሩ ለማድረግ የሚያስችል የንግድ ትርኢቶችን በማመቻቸት ቀጣይነት ያለው ንግድ እንዲፈጠር እና የንግድ ስነምህዳር እንዲሰፋ የበኩሉን አስተዋጾ እያበረከተ እንደሆነ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። እንዲህ አይነት መድረኮችን በማመቻቸት አዲስ ቻምበር እንደ ሞሀን የመሳሰሉ ኩባንያዎች የገበያ እድሎችን እንዲያገኙ በማድረግ የላቀ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ ስለ ምክር ቤቱ መስክረዋል። ስለሆነም ለአዲስ ቻምበር የከፈልኩት ገንዘብ አስር እጥፍ ሆኖ ክሶኛል በማለት ተናግረዋል።

ከነዚህ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች ባለፈም አዲስ ቻምበር ምቹ የንግድ ከባቢ ሁኔታዎች በኢትዮጵያ እውን እንዲሆኑ ቀጣይነት ያለውን የአድቮኬሲ ስራዎችን መስራቱ ሊደነቅ ይገባል ብለዋል ሚስተር ሀርሽ። ሌላው አዲስ ቻምበር የንግዱ ማህበረሰብ በአንድ ላይ እንዲሰባሰብ የጋራ የቢዝነስ ማህበረሰብ እንዲገነባ የጋራ እሴት እንዲኖር እያበረከተ ያለው አስተዋጾ ከፍተኛ ስለመሆኑ ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። በመጨረሻም የንግዱ ማህበረሰብ የአዲስ ቻምበር አባል በመሆን ቀልጣፋ የንግድ አገልግሎትና መረጃ እንዲያገኝ ሚስተር ሀርሽ ጥሪ አቅርበዋል።



**አህመድ መሀመድ የሳይፕ ምክትል ዳይሬክተር**

በአዲስ ቻምበር የአብሮነትና የምስጋና ቀን ላይ በመገኘት ስለ ንግድ ምክር ቤቱ አስተያየታቸውን የሰጡት የሴንተር ፎር ኢንተርናሽናል ፕራይቬት ኤንተርፕራይዝ የምስራቅ አፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር የሆኑት አቶ አህመድ መሀመድ ናቸው። ሳይፕን በመወክል በዝግጅቱ ላይ የተገኙት አቶ አህመድ የተሰማቸውን ደስታ በመግለጽ አዲስ ቻምበር የኢትዮጵያን ንግድና ኢኮኖሚ እድገት ላይ እያበረከተ ያለውን አስተዋጾ አድንቀዋል። ረጅም እድሜን ያስቆጠረው ምክር ቤት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ አህጉር ከሚገኙ ቁልፍ ተቋማት መካከል አንዱ አጋራቸው በመሆን እረጅም አመታትን እንዳስቆጠረ መስክረዋል።

ድርጅታቸው ሳይፕ እንደ አዲስ ቻምበር የመሳሰሉ ተቋማት አቅምን በመገንበት በአድቮኬሲ ፣በቢዝነስ ልማትና በአመራርና አስተዳደር ዙርያ የአቅም ስልጠና እንደሚሰጥ የተናገሩ ሲሆን ከዚህ አንጻር እነዚህ ግቦች እንዲሳኩ አዲስ ቻምበር አስተማማኝ አጋር እንደሆነ መስክረዋል። ምክር ቤቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲሳለጥ እና በመንግስትና በግሉ ዘርፍ መካከል ጥምረት በመፍጠር እያበረከተ ያለውን አስተዋጾ አድንቀዋል።

አዲስ ቻምበር በአጠቃላይ የንግዱ ማህበረሰብ ዋልታ በመሆን የንግዱ ማህበረሰብ ድምጽ እንዲሰማ እያበረከተ ያለው አስተዋጾ ቀላል አይደለም ያሉት አቶ አህመድ በየአመቱ ትልልቅ መድረኮችን በማዘጋጀት በንግዱ ማህበረሰብ መካከል ትስስር እንዲፈጠርና ወቅታዊ የንግድ ሁኔታን ለአባላቶቹ በማዳረስ እያበረከተ ያለውን ጉልህ ሚና አወድሰዋል።